# <u>በአውሮፓ ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ</u>
# <u>የግብዣ ጥሪ</u>

የደርግ ወታደራዊ አምባገነን ቡድን በሀገራችን ለዴሞክራሲና ሰብአዊ መበት መከበር፤ ነጻነትን ለተጎናጸፈ ሰብአዊ ኑሮ ለመኖር፤ የሕዝብ አንድነት በእኩልነት እንዲረጋገጥ፡ ለሕግ የበላይነት፤ ለሀገራዊ ሉዓላዊነትና ለህዝብ ደህንነት ሲሉ የታገሉ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ የዛ ብርቅዬ ትውልድ አባላትን በለጋ እድሜያቸው፡ የተወሰኑቱን ከነወላጆቻቸው ለእስር በመዳረግ “ቀይ ሽብር” ተብሎ በሚጠራው አማካኝነት አሰቃቂ እንግልት፡ በሴት እስረኞች ብልት ውስጥ እንጨት እየጨመሩ በማሰቃየት፡ በጋለ ካውያ በማቃጠል ኢሰብአዊ ድብደባና በደል ከፈጸመባቸው በኋላ በጅምላ ግድያ ሕይወታቸውን ቀጥፏል። የመንፈስ ሥብራት አድርሶባቸዋል። በግርፋት፡ በስለት በመቁረጥ ለአካለ ሥንኩልነት ዳርጓቸዋል። በስቅላትና በጥይት ገድሎ ሬሳቸውን በየአውራጎዳናው በመጣል የሕዝብን የትግል ቅስም ለመስበር በመቀጣጫነት ተጠቅሞበታል። ብዙዎቹን በጥይት ደብድቦ በማይታወቅበት ቦታ እንዲቀበሩ የተወሰኑትን በየጥሻው በመጣል በዱር አውሬ እንዲበሉ አድርጓል። በርካታዎቹን ደብዛቸውን አጥፍቷል። የጠሱ ጽዋም ለቤተሰቦቻቸው በመድረሱ ብዙዎቹን መካን አድርጓቸዋል። ይህ አይነት ኢሰብአዊ ድርጊት አሁንም ጎጠኝነት በተጠናወተው በመለስ አገዛዝ በቀጣይነት እየተካሄደ ይገኛል። እነገለብ ዳፍላ፡ ኃይሌ አባይና ገብረ እግዚአብሄር ወልደሚካኤል(ጋይም) ያለ ምንም ፍርድ በተለያዩ ቦታዎች የተገደሉት፡ ያለ ፍርድ ትዕዛዝ ለእስር የተዳረጉ ቁጥር ስፍር የሌላቸው፡ በርካታዎች ደብዛቸው እንዲጠፋ የተደረጉት እንዲሁም ሌሎቹም የዚሁ ኢሰብአዊ ድርጊትና የመብት ጥሰቶች ምሳሌና ምሥክር ናቸው።

በዚያን ዘመን በሕዝባችን ላይ የደረሰው ግፍና በደል፤ የጅምላ ጭፍጨፋና የድርጊቶቹ አሰቃቂነት፡ በተለይም በተበዳዮቹ ስቃይ የሚስቁና የሚዝናኑ ሆነው በመገኘታቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ወደር የለሽ ለመሆኑ በዛ የታሪክ ሂደት ያለፍን ዜጎች ሁሉ በሀዘንና ቁጭት የምናስታውሰው ነው። በአሁኑ ወቅት ከዛ ሁሉ ስቃይ ሕይወታቸው ሊተርፍ እድል ካገኙት ውስጥ በሞት ሳይቀደሙና ትዝታው ከሕሊናቸው ሳይጠፋ የቃል ምስክርነት ለመስጠት የቻሉትን ማግኘት በርግጥም ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ቅን አሳቢ ለሆኑ ሁሉ መልካም እድል ነው ብንል ሀቁን መናገር እንጂ በሌላ እንደማይተረጎም ሙሉ እምነታችን ነው።

ይህን መሰል ኢሰብአዊ ድርጊት አሁን ባለው ትውልድ ላይ እየደረሰ ያለው እንዲቆም በወደፊቱ ትውልድ ላይም እንዳይፈጸም ለማድረግ ፍቅር፡ ትዕግሥት፡ ርህሩሕነት፡ ቸርነትና ሰብአዊ ክቡርነትን የተጎናጸፉና ሞት ተራምደ ያለፉቸው ዜጎቻችን ሁሉ ታሪኩን ሳይበረዝና ሳይደለዝ ለተተኪው ትውልድ ማሳወቅ ኃላፊነትና ግዴታቸው ይሆናል። በባቢሌ ቶላ በእንግሊዝኛ ተደርሶ በጸጋዬ ገ/መድህን ወደ

አማርኛ የተተረጎመው “አንድ ትውልድ ለመምተር፣ ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ” የተሰኘው መጽሃፍ፣ በአቶ አብዲ አብዱላሂ “ያልታደለው ትውልድ” በተሰኘ ርዕስ የተደረሰው እውነተኛ ታሪክ፣ “የደርግ የእስራት ዘመን” በሚል ርዕስ በአቶ ብርሃኑ ሥርፁ የቀረበው መጽሃፍ ይህንን ሕዝባዊ ጥሪ ለማሳካት በየበኩላቸው ያደረጉት ጥረት በምሳሌነት የሚቀርቡ ናቸው።

በቅርቡ ደግሞ ማን ያውራ የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ ነውና በዛ ትውልድ በርካታ አባላት ላይ የደረሰውን ስቃይ በትውስታ መልክ የሚያሳይ የዚሁ ኢሰብአዊ ድርጊት ሰለባ ከሆኑት፣ በግጥም ቃናቸው የአድማጭን ሕሊና በመሳብ የታወቁትና በርካታ ግጥሞችን በሲዲ በማሳተም ለሕዝብ ያቀረቡት አቶ አሊ ሰኢድም ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን አንድ ፊልም አሰርተው ለሕዝብ እይታ አቅርበዋል። ይህ ፊልም በተለያዩ ቦታዎችም ታይቶ ከፍተኛ አድናቆትን ብቻ ሳይሆን በቅርቡ በኢጣሊያ ሜዴአ በተባለ ከተማ በዚህ አመት በተዘጋጀው “ፊልም ለሰላም” በአለ ትዕይንት ሁለት አለም አቀፍ ሽልማቶችን በማግኘት ከፍተኛ እውቅናን አትርፏል። ይህ ፊልም ብዙዎች በሚያሳዝን ዝምታቸው ውስጥ የቀበሩትን እውነተኛ ታሪክ በሞት ሳይቀደሙ ለባለቤቱ እንዲያቀርቡም ጥሪ የሚያደርግ ነውና ይህንን ፊልም በአውሮፓ በተለያዩ ትላልቅ ከተሞች ለማሳየት ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

በርካታ ለሰብአዊ መብት ተቆርቋሪዎች የባዕድም ሆነ ህገር በቀል የሆኑ እንደ ኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ የመሰሉ ድርጅቶች በተለያዩ መግለጫዎቻቸው እንዳሰፈሩት በበዙ ሺ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች እየተሰቃዩ ይገኛሉ። በመሆኑም ይህ ፊልም በኢትዮጵያ ስለሚገኘው የሰብአዊ መበት ረገጣም ሆነ የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ ለመወያየትና ለመገንዘብ አመቺ ሁኔታ እንደሚፈጥር ምንም ጥርጥር የለንም።

በጀርመን ሀገር በፍራንክፈርት ከተማ

በ 22.08.2009 ዓ.ም. በ 16 ሰአት
በ 23.8.2009 ዓ.ም. በ15 ጀምሮ
Haus der Jugende,
Deutschherrenufer 12
Frankfurt a.Main

በኖርዌይ ሀገር በኦስሎ ከተማ
በ 29 ኦገስት 2009 ዓ.ም. በ 14፡00 — 15፡30 ሰአት
Ebbels gate 1

በተባለው ቦታ ለማሳየት ዝግጅቱ እየተጠናቀቀ በመሆኑ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ይህንን የአደራ ጥሪ አክብረውና በቦታው ተገኝተው ይህን ፊልም እንዲያዩ አዘጋጆቹ በአክብሮት ጋብዘዋል። ከፊልሙ እይታ በኋላም አቶ አሊ ጋር የጥያቄና መልስ ጊዜ እንደሚኖርም ተገልጿል። በዚህ አጋጣሚ በራሳችሁ ላይ የደረሰውን ወይንም ደግሞ በቅርብ ዘመድም ሆነ በትግል አጋር ላይ ሲደረግ ያያችሁትንም ሆነ የሰማችሁትን ለመወያየት አመቺ ሁኔታ በመሆኑ በአካል በመገኘት ትዝታችሁን ብታካፍሉ መልካም ነው እንላለን። የዛን ትውልድ አደራም ከፍ አድርጋችሁ መያዛችሁንም ያመላክተናል።